የሰበር መ/ቁ 49931

ሚያዝያ 21 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የጎሽና እርግብ መለስተኛና አነስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ ባለንብረቶች

ማህበር - ጠበቃ ምክሩ ወልደአረጋይ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ተሰማ ኃይሉ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96"ን" መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው ያሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ የክስ ይዘት ባጭሩ ከአመልካች ጋር ሕዳር 12 ቀን 2002 ዓ.ም በመሰረቱት የስራ ውል በድርጅቱ የፋይናንስ አገልግሎት ኃላፊ ሆነው ሲሰሩ መቆየታቸውን ገልፀው የስራ ውሉ ጥቅምት 19 ቀን 2001 ዓ.ም ከሕግ ውጪ መቋረጡን ጠቅሰው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ፣ የሞባይል ስልክ አበል ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ እንዲከፈል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ያሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሳው ክርክር ተጠሪ የስራ መሪ ስለሆነ የስራ ክርክር ችሎት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም የሚል ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ በስራ አፈፃፀም ላይ ባሳዩት ጥፋትና የብቃት ማነስ ችግር የተሰናበቱ በመሆኑ እርምጃው ሕጋዊ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ለማየት ስልጣን እንዳለው በመግለፅ ዋናውን ክርክርም ተመልክቶ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ወደሚለው ድምዳሜ በመድረስ አመልካች የስድስት ወራት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ጥቅምት 17 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪ በስራቸው ላይ የብቃት ማነስ ያሳዩ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ስንብቱ ከሕግ ውጪ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ተጠሪ በብቃት ማነስ ምክንያት ለስራው ብቁ አይደሉም በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር መታለፉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ተጠሪም በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት ቀርበው የካቲት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገፅ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው መጋቢት 16 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የስራ ስንብቱን እርምጃ ሕጋዊ ነው የሚልባቸውን ምክንያቶች ገልፆ ማስረጃ ጠቅሶ የተከራከረ መሆኑና የበታች ፍርድ ቤቶች የቀረቡት ማስረጃዎች የአመልካች ምክንያት በአሳማኝ ማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን በመግለፅ ውሳኔ የሰጡ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የተቻለው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ማስረጃ ምዘናን መሰረት ያደረገ መሆኑን ነው፡፡ እንደሚታወቀው ይሕ ሰበር ችሎት ስልጣኑ ፍሬ ነገርን የማጣራት ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች በሕግ አተረጓጎም ረገድ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሲፈፅሙ ማቃናት ነው፡፡ ይህም በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 80(3/ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ስር የተመለከተ ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ ነበር የተባለው የስራውን አሰራር የሚገልፅ ነው በሚል ምክንያት ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት የደመደሙት ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቱም አመልካች የተሳሳተ ነው ብሎ ቢከራከርም ተጠሪ ሪፖርቱ በሰነድ ችግር ያልተሟላ ስለመሆኑ በመግለፅ ለአመልካች የገለጸ መሆኑን አረጋግጠው ሂሳቡ የተሳሳተ ነበር ለማለት ያልቻሉ መሆኑን ያመኑበት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ የበታች ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ የማስረጃ ምዘናን መሰረት ያደረገ በመሆኑ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችልበት የህግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ባለመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሌላ በኩል ጉዳዩ በሰበር ችሎቱ እንዲታይ ሲደረግ በጭብጥነት ያልተያዘውን ተጠሪ በስራ ግንኙነቱ ከፍተኛ ችግር ሊፈጥሩ ስለሚችሉ ካሳ ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት በአማራጭ አመልካች በመልስ መልሱ ላይ ጠይቋል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ተጠሪ ካሳ ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ይወሰን ዘንድ ምክንያት ይሆናል ያለው ነጥብ ተጠሪ ለአለቃ የማይታዘዙ ናቸው የሚለው ሆኖ በስር ፍርድ ቤቶች የክርክር ነጥብ ያልሆነ እና በተገቢው ማስረጃም ያልተረጋገጠ ነው፡፡ አንድ ሰራተኛ ወደ ስራ ከሚመለስ በአማራጭ ካሳ ተከፍሎት እንዲሰናበት የሚደረገው በስራ ግንኙነቱ ከፍተኛ ችግር የሚከሰት መሆኑን ፍርድ ቤቱ ሲያምን ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 43(3) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ከድንጋጌው ይዘት በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው ፍርድ ቤቱ የስራ ግንኙነቱ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ይገባል ብሎ ለማመን የሚያስችል በቂ ምክንያት ሊኖር ይገባል፡፡ ያለበቂ ማስረጃና ምክንያት አሰሪ የስራ ግንኙነቱ ችግር ውስጥ ሊወድቅ ይችላል ብሎ ስለተከራከረ ብቻ ድንጋጌውን ተግባራዊ ማድረግ የስራ ዋስትናን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ይሆናል፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ አልፈነዋል፡፡ በአጠቃላይ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 14112 ግንቦት 14 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 80323 ጥቅምት 10 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## <u>ት እ ዛ ዝ</u>

በዚህ ችሎት ሕዳር 30 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ